# በሱዳን የሚታተመው የኢትዮጵያ የብር ኖቶች!!!

**August 8, 2017 12:59**

Ethiopian Currency printed in Sudan

## ፀ/ት ፂዮን ዘማርያም

ሱዳን ከረንሲ ፕሪንቲንግ ፕሬስ፤ Sudan Currency Printing Press (SCPP)

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ገንዘብ የብር ህትመት በኢትዮጵያ ገንዘብ ለማተም ዕቅድ በማውጣት የብር ማተሚያ ፋብሪካ በሣይንሳዊ መንገድ፣ የወንጀል ማጭበርበር ሥራዎች እንዳይከሰት ሚስጢራዊ የህትመት ዘይቤንና የህዝብና የሃገር ደህንነትና ህልውና የሚያረጋግጥ ማተሚያ ፋብሪካ ለመገንባት በኢትዮጵያ ሄራልድ ዲሴንበር 2/2014 እኤአ በወጣው ጋዜጣ ላይ ዓለም ዓቀፍ አማካሪ ድርጅቶች ጥናት እንዲያቀርቡ የገንዘብ ማተሚያ  ፍብሪካን በሚመለከት በጨረታ ጋብዞ ነበር፡፡

የብሄራዊ ባንክ የገንዘብ ማተሚያ ፋብሪካውን ለማቆቆም ዋነኛ አላማዎቹ ውስጥ በባህር ማዶ ሃገር ገንዘብ ለማሳተም የሚወጣዉን የውጪ ምንዛሪ ለመቆጠብ፣ የብር ህትመትን በአንድ መዕከል ሥር ለማድረግና ለመቆጣጠር እንዲሁም ከሁሉም በላይ ለህዝብና ለለሃገር ብሄራዊ ደህንነት፣ ለሃገር ሉዓላዊነት፣ብሎም ከበዓድ ሃገር ይልቅ፣ በራስ የመተማመን ዋስትና ለማዳበር የሚሉት ዓላማዎች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የገንዘብ ማተሚያ ፋብሪካና ግንባታ ትልቅ የኢንቨስትመንት ወጪ የሚጠይቅ ሲሆን ለዚህ ሥራ ዘመናዊ ተምህርትና ክህሎት ያለው ፣የተማረ የሰው ኃይል ማሠልጠን ደግሞ ሌላው ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ማለትም የኢንቨስትመንት ወጪና በዘርፉ የሠለጠነ የሰው ኃይል በሃገር ውስጥ አለመኖር የተነሳ፣ሃገራችን በባህር ማዶ አገራቶች ገንዘብ ለማሳተም ተገዳለች፡፡



1932 birr 1961 birr 1969 birr

በመሠረቱ ለአንድ አገር ዘርፈ ብዙ የገንዘብ ማተሚያ ፋብሪካና ግንባት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የሃገሪቱን ሉዓላዊነት ለመጠበቅና ሚስጢራዊ የህትመት ሥራዎች ለመከወን ዘርፈ ብዙ ማሽኖች የገንዘብ ብር ማተሚያ ማሽን (Banknotes Printing Machines)፣ የንግድ ህትመት ሥራዎች (Commercial Printing Machines)ና የዲጂታል ህትመት ሥራዎች (Digital Printing Machines) ዘመናዊ ፋብሪካዎችን በመትከል፣ በህትመቱ ሥራ፤  የብር ኖትና የቼክ ደብተር፣ የፓስፖርትና የሃገር ውስጥ መታወቂያ ካርዶች፣ የቀረጥ ቴንብር፣ የፖስታ ቴንብር፣ የሎተሪ ትኬት፣ የሞባይል ካርዶች፣ ልዩ ልዩ የዩኒቨርሲቲና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህጋዊ ሰርተፊኬቶች፣ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣ መንጃ ፍቃድ፣ ፖስተሮች ወዘተ ቢሰራ የማተሚያው ፋብሪካ አስተማማኝ ሥራ፤ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በማህበራዊ ዘርፎች በተለይም በህዝብና ሃገር ደህንነት ታላቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ሚስጢራዊ የህትመት ሥራ አስፈላጊነት በአጠቃላይ ገንዘብ፣ ልዩ ልዩ ሰነዶች፣የባለሥልጣን ፊርማዎች ወዘተ አስመስሎ በሚሠሩ ህገወጥ ሰዎችና ድርጅቶች በቀላሉ እንዳይሰራና፣ በፎቶ-ኮፒ መልክ እንዳይባዛ፣ለዓዕምሮዊ የፈጠራ ሥራ እውቅና የሚሠጥ፣ጥበቃና ከለላ የሚያላብስ፣ መቅዳትና መኮረጅ ነውር ሥራ መሆኑን የሚያስተምር፣ በመሆኑ የህብረተሰቡን ባህል የሚያዳብር፣ የሰው ልጆችን ታሪካዊ ቅርስና ውርስ የሚያስጠብቅ፣መልካም ሥነምግባርና ግብረገባዊ እሴቶች እንዲቀጥል ትልቅ ሚና የሚጫወት፣ ዘመናዊና ሳይንሣዊ ሚስጢራዊ የህትመት ሥራ ከህግ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የወንጀል ሥራዎች፣ እውነቱን ከውሸቱ ለመለየት የሚያስችል በመሆኑ፣ሳይንሳዊ የህትመት ሥራና ማስረጃ በሃገራችን መጀመር አለበት፡፡

Secured Documents are those protected against counterfeit or forgery. Protection is not done exclusively through the use of water mark only but also by using new technology, materials and the type of printing. Those documents comprises : Passports, nationality certificates, university certificates, secondary school certificates, elementary education certificates, duty stamps, postal stamps and many others.

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ኃላፊት

.የገንዘብ አቅርቦት መመጠንና አስፈላጊነቱን መቆጣጠር፣የገንዘብ ወጪና ብድርን መወሰን መጠበቅ

.የሃገሪቱን የዓለም ዓቀፍ ተቀማጭና መጠባበቂያ ገንዘብ መቆጣጠርና ማስተዳደር

.ለባንኮች ፍቃድ መስጠትና መቆጣጠርና ክትትል ማድረግ፣የንግድ ባንኮች ተቀማጭ መያዝ፣

.እንዲሁም ለንግድ ባንኮች ገንዘብ ማበደር፣

.የንግድ ባንኮችን ብድር መቆጣጠርና ክትትል ማድረግ እንዲሁም የወለድ መጠንን መወሰን፣

.የብር ኖቶችንና ሣንቲሞችን ማውጣት፣

.እንደ መንግሥት ወኪል ሆኖ መስራት፣

.የውጭ ምንዛሪ ምጣኔን መወሰንና መቆጣጠር፣
በአጠቃላይ ‹‹ብሔራዊ ባንክ ምንዛሪ ያሠራጫል፣የአገሪቱን የውጪ ምንዛሪ መጠባበቂያ ይይዛል፣ለውጭ ኢኮኖሚ ግንኙነት የክፍያ ሚዛን ዓላማ ይበደራል፣የመንግሥት ባንክ ሆኖ ይሠራል፣የመንግሥት ሠነዶችን ግዥና ሽያጭ ያካሂዳል፣ለመንግሥትና ለንግድ ባንኮች ያበድራል፣የውጭ ምንዛሪ ይገዛል፣ይሸጣል፣ የጥሬ ገንዘብን መጠን ለመቆጣጠር ሕግ ያወጣል፣ የባንኮች ባንክ ሆኖም ይሠራል፡፡›› የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ኃላፊዎች ኃላፊነታቸውን መወጣት ያልቻሉ፣ የሃገሪቱን የብር ኖቶች በሱዳን የግል የገንዘብ ማተሚያ ቤት በማሳተም የሃገሪቱን ሉዓላዊነት አሳልፈው የሸጡ የባንክ ሙያተኞች ናቸው፡፡ የሃገሪቱ ብሄራዊ ደህንነትና ኢኮኖሚ በድንበር ዘለል ንግድ የቁም እንሰሳት፣ ወርቅ ማዕድን፣ የጫት ንግድ፣ የቅባት እህሎች ንግድ ወደ ጎረቤት ሃገሮች በመሸጥ ከወያኔ ጋር ተመሳጥረው በመዝረፍ ሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡

# ኢትዮጵያ የብር ኖቶች ህትመት አጭር ታሪካዊ ዳሰሳ

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የገንዘብ የብር ኖቶችን የሚያሳትመው በምድረ አውሮፓ የነበረ ሲሆን በተለይም በሃገረ-እንግሊዝና ፈረንሳይ እንደሆነ በታሪክ ይታወሳል፡፡ ብሄራዊ ባንክ አዲስ ብሮች እንዲታተሙለት ትዕዛዝ ያስተላልፋል፣አንዳንዴም ያረጁ ብሮችን ከገንዘብ ዝውውሩ ለማስወጣትና በምትካቸው አዲስ የብር ኖቶች በማሳተም አሮጌ ብሮችን ያቃጥላል፡፡ ብሄራዊ ባንክ የግል ባንኮች የቼክ ደብተር ህትመት ብሄራዊ ባንክ ማተሚያ ቤት እንዲያሳትሙ ትዕዛዝ በመስጠትና የቼክ ማጭበርበር ወንጀል እንዳይሰራ ባንኮቹ አንድ ዓይነት የድህንነት ሚሥጢራዊ የቼክ ህትመት እንዲኖራቸው ያደርግ ነበር፡፡

Accordingly all checkbooks issued by every Ethiopian banks will be printed centrally through the National Bank of Ethiopia following a standardized format

ከ 18 እስከ 19 ክፍለ ዘመን ማርያ ቴሬዛ ታላሪ እና ጥፍጥፍ አሞሌ/ጨው እንደ ገንዘብ ያገለግሉ ነበር በዳግማዊ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት በ 1893/94 እኤአ 200000 ታላሪ /ዶላር በፓሪስ የሳንቲም ገንዘብ ተሠራ

ከ 1931 በፊት የአቢሲኒያ ብር በሚል ሲታወቅ ባንኩም የአቢሲኒያ ባንክ 1905/6 እኤአ በአፄ ሚሊኒሊክ ተመርቆ፣ ከአውሮፓ ባንኮች ጋር አብሮ በመስራት 1200000 የሳንቲም ገንዘቦች በየአመቱ ወደ ሃገራችን ይገባ ነበር· በ 1915 እኤአ የአቢሲኒያ ባንክ የወረቀት ገንዘብ ብር ወይም ታለር ማሳተም ጀመረ First birr]The Bank of Abyssinia introduced banknotes for 5, 10, 100 and 500 talari in 1915. 280,000 talari worth of notes was printed. The text on the notes was in Amharic and French. A 50-talari note was added in 1929, by which time over 1.5 million talari in notes were circulating.

በ 1931 እኤአ በአፄ ኃለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የአቢሲኒያ ባንክ በ 235000 ፓውንድ በመግዛት የኢትዮጵያ ብር በሚል ሲታወቅ ባንኩም የኢትዮጵያ ባንክ በመባል ይጠራ ነበር

ከ 1936 እስከ 1941 እኤአ በኢጣልያን ወረራ ዘመን፣ የጣሊያን ሊሬ (Italian lira) በባንካ ደ ኢታሊያ (Banca d’Italia) የጣልያን ሊሬና ሳንቲሞች በሃገሪቱ ተሠራጩ፣ ብዙ ህዝብ የኢትዮጵያን ብርና ሣንቲሞች ደብቆ አስቀመጠ፡፡

በ 1945 እኤአ ሁለተኛው ብር ዳግም ተሰተወወቀ በዚህም መሠረት አንድ ብር የሁለት ሽልንግ እኩሌታ ነበረው፡፡

በብሩ ላይ የኢትዮጵያ ዶላር የሚል በእንግሊዘኛ ተፅፎበት ነበር፡፡

ከ 1976 እኤአ ጀምሮ ብር በይፋ በሁሉም አገራት ቆንቆ የኢትዩጵያ ብር መጠሪያ ስያሜውን አገኘ፡፡

ከ 1976 በፊት የኢትዩጵያ ዶላር በሚል ይታወቅ ነበር

ከ 1976 በኃል እስከ አሁን ድረስ የኢትዩጵያ ብር በሚል ይጠራ ጀመር

በ 2008 እኤአ 186 ቢሊዩን ብር (14.7 ቢሊዩን ዶላር ወይም 9.97 ቢሊዩን ፓውንድ) በሃገሪቱ የገንዘብ ዝውውር ውስጥ ይካሄድ ነበር፡፡

የኢትዩጵያን ሣንቲሞች ዓይነቶችን ለመለየትና በአፈታሪክ የሚነገሩትን ዘርዘር አድርገን ዳሰን እናልፋለን፡፡

ከ 1969 እንደ ኢትዩጵያዊያን አቆጣጠር በፊት ያሉ ሣንቲሞች ዘውድ ያደረገ አንበሣ መስቀል ይዞ ተሸክሞ ይታይ ነበር፡፡ በቀ.ኃ.ሥ ዘመን የነበረው አንበሣ የጠገበ በመሆኑ አፍን ዘግቶ ይታያል፡፡

ከ 1969 እንደ ኢትዩጵያዊያን አቆጣጠር በኃላ ያሉ የሃገሪቱ ሣንቲሞች ባለ ጎፈር አንበሣ ሲያገሣና ሲጮህ የሚያሳይ ሆነ፡፡

በወታደራዊው ደርግ ዘመን የነበረው አንበሣ ያልጠገበ በመሆኑ አፍን ከፍቶ ጥርሶቹን አግጦ ሊበላን ነው ያሉ ቁስ በአፍ እላፊ ተከሰው ወህኒ ቤት እንደወረዱ ይነገራል፡፡ በሣምሳ ሳንቲሙ ላይ ያለ ምስልን ደግሞ በወታደሩ ጠመንጃ የተማረኩ እጃቸውን ወደላይ ያደረጉ ቀንበር የያዘ ገበሬ፣ መዶሻ የያዘ ላብአደር፣ ብዕር የያዘ ተማሪ፣ ማጭድ የያዘች ሴት ናቸው እየተባለ፡፡ ሣንቲሞች ተሠርተው የመጡት ከፓሪስ፣በርሊን፣ እና አዲስ አበባ ሣንቲም መቅረጫ ፋብሪካ ነው፡፡

በወታደራዊው ደርግ ዘመን የነበረው የአንድ ብር ኖት ዘቅዝቀው ሲያዩት በዛፎቹና ቁጥቆጦዎቹ ሥር ኢህአፓ የሚል ምህፃረ ቃል አንዱ ለአንዱ ሲያሳይ በጊዜው በዚህ ምክንያት የታሠሩ ተማሪዎች ነበሩ፡፡

በህወኃት/ኢህአዴግ ዘመን የአንድ ብር ሣንቲም ተጀመረ፣ በሣንቲሙ አንድ ጎን እንደ ደርግ ዘመን ያለ ያልጠገበ አንበሣ፣ አፍን ከፍቶ ጥርሶቹን አግጦ ሊበላን ነው ሲያስብለን በሳንቲሙ ሌላ ጎን የፍርድ ሚዛን ያሳያል፣አንበሣው የሚበላህ በፍርድ ነው ዓይነት መልዕክት ያስተላልፋል፡፡ በዚህም ምክንያት ይመስላል ተቃዋሚዎች ህወኃትን ‹‹የውስጥ አንበሣ የውጪ ሬሣ!!!›› የሚሉት፡፡

# ኢትዩጵያ የብር ኖቶችን በሱዳን ለማሳተም እየመረመረች ነው

በጁላይ 31/ 2013 እኤአ ርዕሰ አንቀፅ መሠረት የኢትዩጵያ ብሄራዊ ባንክ የብር ኖቶችን በሱዳን የገንዘብ ማሳተሚያ የግል ካንፓኒ ለማሳተም ሁኔታዎቹን እየመረመረ መሆኑና ለሱዳን ማዕከላዊ ባንክ ገንዘብ በማተም ላይ ይገኛል፡፡

Ethiopia investigating printing its birr notes in Sudan Aug 01, 2013 09:01 AM Category: Africa According to a Daily Ethiopia article dated 31 July 2013, the National Bank of Ethiopia (NBE) is considering having its birr banknotes printed by the Sudan Currency Printing Press (SCPP), a private enterprise established in 1994 which prints all Sudanese currencies for the Central Bank of Sudan. Currently the NBE utilizes unnamed European companies to print its birr notes. NBE to print birr notes in Sudan By Staff Reporter – July 30, 2013

የኢትዩጵያ ብሄራዊ ባንክ የብር ኖቶች በሱዳን ለማሳተም ወጠነ በሚል ርዕስ በጁላይ 30 2013 እኤአ ካፒታል ጋዜጣ ታትሞ ወጥቶ ነበር፡፡ የሙያው ሰዎች ወደ ሱዳን በመጎዝ የሱዳን የገንዘብ ማተሚያ ካንፓኒ ኃላፊነቱ የተወሰነ ድርጅትን ጎብኝተዋል፡፡ የብርሃነ ሰላም ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣በጉብኝቱ ወቅት የህትመት ማሽኖችና የካንፓኒው ችሎታን ለማየት ችለዋል፡፡ ካንፓኒው በሱዳን ውስጥ ብቸኛ ፍቃድ ያለው የግል ድርጅት ሲሆን ሁሉንም የሱዳን የገንዘብ ህትመት በማከናወን የማዕከላዊው ሱዳን ባንክ ደንበኛ ነው፡፡

የካንፓኒው ህትመት ማሽን አዲስ የቴክኖሎጅ ውጤት የገንዘብ ማተም ጥበብ ረቂቅነት የሚታይበት ነው፡፡ ባለፉት ጊዜት የኢትዩጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ የብር ኖቶች በማሳተም በሚሊኖች ዩሮ የሚቆጠር ወጪ ለአውሮፓ የገንዘብ ማተሚያ ካንፓኒዎች ነበር፡፡ የኢትዩጵያ ብሄራዊ ባንክ፣ከአውሮፓ የገንዘብ ማተሚያ ካንፓኒዎችን ትቶ በሱዳን ከረንሲ ፕሪንቲንግ ፕሬስ የብር ኖቶችን ማሳተም መጀመሩ እንቅቅልሹን የብሄራዊ ባንክ ገዥውና ህወኃት የጦር አበጋዞች መንግሥት ሴራን የባንኩ ሙያተኞች ለህዝብ ማሳወቅና ማጋለጥ ታሪካዊ ግዴታ አለባቸው፡፡
ሱዳን ከረንሲ ፕሪንቲንግ ፕሬስ፤ Sudan Currency Printing Press (SCPP)

የሱዳን የገንዘብ ማተሚያ ፕሬስ፤ኃላፊነቱ ተወሰነ የግል ኢንተርፕራይዝ በግንቦት 1994 እኤአ መጨረሻ ላይ የተመሰረተ የግል ድርጅት ሲሆን በሃገሪቱ የ 1925 እኤአ የካንፓኒዎች ህግ መሠረት የተቆቆመ የሃገረ ሱዳን የገንዘብ ማተሚያ ፋብሪካ ነው፡፡

Sudan Currency Printing Press (SCPP) is a private enterprise of limited liability established in May 1994 in accordance with the 1925 company law. The Company had started the real production at the end of 1994.

የሱዳን የገንዘብ ማተሚያ ካንፓኒ ዋነኛ ተግባሩ የገንዘብ ኖቶችን በማተም፣ በሱዳን ውስጥ ባለሙሉ ሥልጣን የማተሚያ ድርጅት ነው፡፡ ካንፓኒው የሱዳን ብሄራዊ ባንክን የገንዘብ ኖቶች አቅርቦትና ፍላጎት በማሞላት፣ በብቃት በቴክኒክና በጥራት አገልግሎት አበርክቶል፡፡እንዲሁም ካንፓኒው ለማእከላዊው የሱዳን ባንክ አማካሪ ድርጅት በመሆን ዘመናዊ የቴክኖሎጅና የገንዘብ ህትመት ጥበቦችን በማዘመን አስተዋፅኦ አድርጎል፡፡ የካንፓኒው በገንዘብ ኖቶች ህትመት ላይ የጀመረው በመንግሥት መመዘኛና መሥፈረት መሠረታዊ ድጋፍ ለብሄራዊ ሉዓላዊነታችን በመፅናትና በእራሳችን ዘርና ድጋፍ ላይ የተመሠረተ መኖሪያ ቤት በማነፅ፣ በእራሳችን ላይ ለመተማመን ነው፡፡

Banknotes production is the main activity of the company as the name indicates (Sudan currency printing press). The company is the unique authorized of printing banknotes in Sudan. It supplies all the needs of the central banks, in a high technical and secured quality, Also the company serves as a consultant to central bank by acquainting the latter with the latest innovations in currency printing. Its activity in banknotes printing began within the framework of the government to build basic supports to fulfill the national sovereignty, and planting supports of settlement and self-dependence.

## የሱዳን የገንዘብ ማተሚያ ፕሬስ፤ዋና ዋና ተግባራት መኃል፣

ለተለያዩ ሃገሮች ባንኮች ገንዘብ ማተም (banknotes)፣ ቼክ ማተም፣ለኢንሹራንስ ካንፓኒዎች የኢንሹራንስ ስርቲፊኬቶች ማዘጋጀትና የባንኮች ዶክመንቶች ህትመት ማዘጋጀት እንዲሁም ለውጪ ሃገሮች የተለያዩ የህትመት ሥራዎች መሥራት

ለአገር ውስጥና ለባህር ማዶ ሃገሮች የአገር ግዛት ሚኒስትር መስሪያ ቤት (Ministry of Interior) ፓስፖርቶችና፣ከሃገር መውጫና መግቢያ ቪዛ፣ፓስፖርት ላይ የሚመታ የሚያብለጨልጭ የቪዛ ስቲከር ብሄራዊ ዶክመቶች፣ መታወቂያ ካርዶችና የተለያዩ የመታወቂያ ዶክመንቶች ማሰናዳት፣ የትራፊክ አስተዳደር ህትመቶች ማዘጋጀት

ለአገር ውስጥና ለውጪ ሃገራት የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስትር መስሪያ ቤት (Ministry of Finance and National Economy )

የገንዘብ ፎርም፣የመንግሥት ገቢ ደረሰኞች ማዘጋጀት

ለአገር ውስጥና ለባህር ማዶ ሃገሮች ፖስታና ቴሌግራም መንግሥታዊ ኮርፖሬሽኖች ( The Postal and Telegram Public Corporation)

የፖስታ ቤት ቴንብሮች (postal stamps) የቀረጥ ቴንብር (duty stamps) ማተም፣

የሞባይል ካርዶች፣ የሎተሪ ካርዶች ማተም

ለተለያዩ ሃገሮች የሃጅና ኡምራ የእስልምና እምነት ተጎዦች የሃይማኖት ተቆማት (The Hajj and Umra Public Corporation)

የሃጅና ኡምራ ተጎዦች የመታወቂያ ካርዶች ማዘጋጀት

ለባህር ማዶ ሃገራት የግብርና ታክስ (Taxes Department) የታክስ ቴንብሮች ማተም

ለሃገር ውስጥና ለውጪ ሃገሮች የመንግሥትና የግል ዩኒቨርሲቲዎችና አካዳሚክ ስርቲፊኬቶች፣ዲግሪ፣ዲፕሎማ ሰርቲፊኬት፣

የልደትና የሞት ስርተፊኬት፣

የመኪና፣የሞተረ ሳይክል መንጃ ፍቃድ ወዘተ ህትመት ሥራዎች ማዘጋጀት

ለተለያዩ ሃገሮች ካንፓኑዎች የበጀት፣ ፖስተሮች፣ ፎልደሮች፣መፅሃፍትና መጋዚኖች ማተምና ማዘጋጀት እንዲሁም ለመንግሥትና ለግል ካንፓኒዎች ዘመናዊ ማህተም መቅረፅና ሌሎችም ተግባራት ያከናውናል፡፡

ለተለያዩ ሃገሮች ካንፓኒዎች የንግድ ህትመት ሥራዎች( Commercial Printing Machines)ና የዲጂታል ህትመት ሥራዎች( Digital Printing Machines) መስራት የመሳሰሉትን ተግባራት በማከናወን የደለበ የውጪ ምንዛሪ ያስገኛል፡፡

ኦማር ሃሰን አል-በሽር፣ Omar Hassan al-Bashir

ኦማር ሃሰን አል-በሽር ከ 1989 እኤአ አቆጣጠር ጀምሮ በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት የሱዳን ፕሬዜዳንት በመሆን ላለፉት 28 ዓመታት በአንባገነንነት ሱዳንን የገዙ መሪ ናቸው፡፡ በዓለም ዓቀፍ ፍርድ ቤት በጦር ወንጀል፣ በኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ወንጀል፣በ 2003 እኤአ በዳርፉር የዘር ማጥፋት ወንጀል ሁለት መቶ ሰዎች የግድያ ወንጀልና በሁለት ሚሊዩን ሰዎች መፈናቀል ክስ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲያዙ ትእዛዝ የወጣባቸው ወንጀለኛ መሪ ናቸው፡፡ አል-በሽር በምድረ-ሱዳን ህዝብ ላይ በድንበር ዘለል ግጭት፣ በፖለቲካ አለመረጋጋት፣ በደካማ መሠረተ-ልማት፣ እና በሙስና ሃገራቸውን ያደህ መሪ ናቸው፡፡ በ 2011 እኤአ የደቡብ ሱዳን መገንጠል በኃላ፣ሱዳን ሁለት ሦስተኛ ነዳጅ ገቢዎን ደቡብ አጥታለች፡፡ በ 2015 እኤአ የተባበሩት መንግሥታት ሪፖርት መሠረት የዳርፉር ግጭት የዓለም ዓቀፍ ህብረተሰብ ትኩረት አገኘ፡፡ በ 2015 እኤአ ዓለም ዓቀፍ የግልፅነት መለኪያ ድርጅት መረጃ መሠረት፣ የሱዳን መንግሥት ከዓለም አገራት በሙስና ከ 168 አገራቶች 165 ኛ ደረጃ ላይ የተፈረጀ ሙስኛ መንግስት ነው፡፡ አል-በሽር መንግሥት የፖለቲካ ስልጣንና የተፈትሮ ኃብት በካርቱምና በአካባቢው በመሰብሰብ ቀርውን የሱዳን ህዝብ በድህነት አረንቋ ውስጥ በመዝፈቅና የሃገሪቱን ኢኮኖሚ መቀመቅ የከተተ መንግሥት ነው፡፡

“Omar Hassan al-Bashir has been president since 1989 after coming to power in a military coup. He faces two international arrest warrants based on charges of war crimes, crimes against humanity, and genocide in the Darfur conflict that has killed over 200,000 people and displaced over 2 million since 2003. Cross-border violence, political instability,poor infrastructure, weak property rights, and corruption hinder development. Following the secession of South Sudan in 2011, Sudan lost two-thirds of its oil revenue to the South. A June 2015 U.N. report of anupsurge of violence in Darfur has raised concerns that the conflict may be heating up again. Sudan, one of the world’s most corrupt nations, was ranked 165th among the 168 countries surveyed inTransparency International’s 2015 Corruption Perceptions Index. Power and resources are concentrated in and around Khartoum, while outlying states are neglected and impoverished.”

Source:- Sudan Economy Population, GDP, Inflation, Business, Trade, FDI, Corruption.mht

© 2017 by The Heritage Foundation. All Rights Reserved

የአሜሪካ መንግስት አጠቃላይ የኢኮኖሚ እቀባ በሱዳን መንግሥት ላይ ጥሎል፡፡ በዚህም ምክንያት ሱዳን ከነዳጅ ሌላ የገቢ ምንጮን ለማዳበር የወርቅ መእድን፣ ጋም አረቢክ/ሙጫ ከ 75 እስከ 80 በመቶ የዓለም ምርት በማምረት ገቢዎን ለማዳበር ትፍጨረጨራለች፡፡ በሱዳን በግብርናው ዘርፍ 80 በመቶ ህዝብ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡ ሱዳን ‹‹የሱዳን ፓውንድ›› መጠሪያ አዲስ ገንዘብ ብታትምም፣ ‹‹የሱዳን ፓውንድ›› የውጪ ምንዛሪ ተመኑ በየጊዜው እየወደቀ ይገኛል፡፡ በ 2012 እኤአ ሱዳን የገንዘብ ተመኖን በማርከስ ኢኮኖሚዋ በማዕቀቡ ተሽመድምዶል፡፡ በዚህም ምክንያት የሱዳን መንግሥት የነዳጅ ድጎማ ፖሊሲውን አንስቶል፡፡ በ 2012 እኤአ ሱዳን በ 47 በመቶ የዋጋ ግሽበት ስትመታ በ 2016/17 እኤአ የዋጋ ግሽበቱ 20 በመቶ ዝቅ ብሎል፡፡

የህወኃት የጦር አበጋዞች መንግሥት ከሱዳን ወሮበላ መንግሥት ጋር በማበር የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅምና፣ የሃገሪቱን የግዛት ሉዓላዊነት አሳልፎ ለሱዳን በመስጠት የተወዳጀ ዘረኛ መንግሥት ነው፡፡ የአል-በሽር መንግስት የኢትዮጵያ ተቃዎሚዎችን አሳልፎ ይሰጣል፡፡ የአል-በሽር መንግስትና የህወኃት የጦር አበጋዞች መንግሥት እጅና ጎንት ሆነው በሃገራችንና ህዝቦ ላይ ሲያሴሩ አመታት ተቆጠሩ፡፡ በህዝባዊ ትግል የባርነት ሠንሰለታችንን እንበጣጥስ፡፡

Sudan is also subject to comprehensive US sanctions. Sudan is attempting to develop non-oil sources of revenues, such as gold mining, while carrying out an austerity program to reduce expenditures. The world’s largest exporter of gum Arabic, Sudan produces 75-80% of the world’s total output. Agriculture continues to employ 80% of the work force.
Sudan introduced a new currency, still called the Sudanese pound, following South Sudan’s secession, but the value of the currency has fallen since its introduction. Khartoum formally devalued the currency in June 2012, when it passed austerity measures that included gradually repealing fuel subsidies. Sudan also faces high inflation, which reached 47% on an annual basis in November 2012 but subsided to about 20% in 2016-17.

{1} ሱዳን ለኢትዩጵያ መንግስት የነዳጅ ፍጆታ ሺያጭ፣Sudan oil export to Ethiopia በአሁኑ ወቅት በአጠቃላይ የሃገሪቱ አመታዊ የነዳጅ ፍጆታ  ሶስት ሚሊዩን ሜትሪክ ቶን የደረሰ ሲሆን መንግስት በዓመት ለነዳጅ ግዢ 2.8 ቢሊዩን ዶላር ወጪ ያደርጋል፡፡የኢትዩጵያ መንግስት ከኩዌት ጋር በገባው ውል የአውሮፕላን ነዳጅ 710000 ሜትሪክ ቶን፣ ናፍጣ 1.2 ሚሊዩን ሜትሪክ ቶን፣(60 በመቶ) ከኩዌት ፔትሮሊየም ኮርፖሬሽን ይሸምታል፡፡ ከሱዳን መንግስት ደግሞ፣አጠቃላይ ቤንዚን ፍጆታ 193000 ሜትሪክ ቶን፣ (85 በመቶ) የሚሆነውን ከሱዳን መንግስት ይሸምታል፡፡

የነዳጅ የገቢ ንግድ ወጪ(Fuel Imports)

| | የነዳጅ የገቢ ንግድ ወጪ |
|---|---|
| 2006 | 860.4 |
| 2007 | 875.1 |
| 2008 | 1,621.4 |
| 2009 | 1,256.7 |
| 2010 | 1,310.7 |
| 2011 | 1,659.3 |
| 2012 | 2,124.7 |
| 2013 | 2,163.8 |

ለምሳሌ፤ በ 2012/13 የነዳጅና ዉጤቶች 1,466,114,603 ቢሊዩን ዩኤስ ዶላር በገቢ ንግድ ወደሃገር ተከፍሎ ገብቶል፡፡ ለመጭው አመት ሦስት የውጭ ባንኮች(ኢንተርናሽናል ፋይናንሻል ኮርፖሬሽን(አይኤፍሲ)፣የፈረንሳዩ ኢንቨስትመንት ናቲክሲስ ባንክና ስታንደርድ ባንክ ግሩፕ) ለኢትዩጵያ ዓመታዊ የነዳጅ ወጪ የሚውል 500 ሚሊዩን ዩኤስ ዶላር የብድር አገልግሎት ሰኔ 2014 እኤአ ብድር ተገኘ ነው፡፡ ለሃገሪቱ የሚያስፈልጉ የገቢ ንግድ መግዣ በተለይ የነዳጅ ፍጆታ ከ 2.5 እስከ 3 ቢሊዩን ዶላር ወጭ ከፍሎ ማስገባት ስለማይቻል በነዳጅ የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ሁሉ ለመቆም ይገደዳሉ፡፡የዋጋ ግሽበት፣ ህዝብ የግብርና ምርትና ወደ ገበያ ካላወጣና የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦች እጥረት ካለ የዋጋ መናር ያስከትላል፡፡ የኦሮሞና የአማራ ክልል ህዝባዊ እንቢተንነት ትግል  ያመረተውን ምርት ወደ ገበያ ባለማውጣትና ድንበር ዘለል ንግድ ወደ ሱዳን፣ሱማሌ፣ኬንያና ጅቡቲ እንዳይሄድ ካገደና ትግሉን ከቀጠለ በሃገሪቱ የውጪ ንግድ ገቢ ኢምንት ሆኖ የውጭ ምንዛሪ እጦት ይፋጠራል፡፡

በዚህም ሃገሪቱ ያለባትን የብድር ወለድ የመክፈል አቅም አይኖራትም፡፡

{2}የሱዳን የቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በኢትዩጵያ፣Sudanese DFI Investment in Ethiopia በኢትዩጵያ የውጪ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በመጀመሪያ ደረጃ 207 የቻይና ፕሮጀክቶች፣ በሁለተኛ ደረጃ 152 የህንድ ፕሮጀክቶች፣በሦስተኛ ደረጃ የሱዳን ፕሮጀክቶች፣ እንደሆኑ የኢትዩጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ኮሚሽን ኮሚሽነር ፍፁም አረጋ ገልፀዋል፡፡

Ethiopia remains the prime choice for FDI, 08 November 2016, ethioinvest@investethiopia.gov.et ”Over the recent years Ethiopia has become highly attractive for foreign investment, especially among countries such as China, India, Turkey and Sudan. These countries remain among the top three investors in the country.
China ranks top in foreign direct investment in Ethiopia. Chinese projects currently stand at 207 leading India by over 152 more projects. China is followed by India and Sudan in 2nd and 3rd place with the highest foreign direct investment according to the information secured from the Public Relations Directorate.” Fitsum Arega, the Ethiopian Investment commission Commissioner. (http://www.investethiopia.gov.et/)

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ሪፖርት መሠረት በ 2008 ዓ/ም እኢአ በኢትዮጵያ የውጭ ባለሃብቶች ተሳትፎ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍእድገት ማሳየቱን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡ በተለይ የአረብ አገራት ባለሃብቶች ተሳትፎ ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ መምጣቱን አስታውቀዋል፡፡ በዚህም መሠረት በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ፡-

ተ.ቁ

የአረብ አገራት ባለሃብቶች

1 ከተባበሩት አረብ ኢሚሬት 33

2

ከሳውዲ አረቢያ

106

3

ከሱዳን

56

ለውጭ ባለሃብቶች የሚሰጠው ማበረታቻ በተለይ መሬት፣ የግብር እፎይታና ከቀረጥ ነፃ እቃዎችና እንዲያስገቡ በመደረጉ የውጭ ባለሃብቶች ቁጥር እንዲጨምር አድርጎል፡፡”

During the second GTP II has planned 1349 foreign investors to start operation in Ethiopia. the figure exceeded the set target of bringing 1200 investors. (GTP II FDI)”

{3}ሱዳን ከኢትዮጵያ ድንበር ዘለል የቁም እንስሳት ንግድ ድርሻ

ከኢትዮጵያ ከመካከላኛው ምስራቅ አገራቶች አንፃር በቁም እንስሳትና የሥጋ ውጤቶች ንግድ ትልቅ ጥቅምና ብልጫ ያላት ሃገር ስትሆን የቆላማው ዝርያ በተለይም የቦረና በሬና የሱማሌ ጥቁር ጭንቅላት ያላቸው በጎች ዝርያ በብዙ ደንበኞች ተወዳጅ ናቸው፡፡ ወደ ውጪ የሚላኩ 1.6 ሚሊዩን የቁም እንስሳት በአመት ወደ ባህር ማዶ ገገራት በተለይም የገልፍ አገራትና ግብፅ ይላካል፡፡ የሚገርመው ታዲያ ከዚህ ውስጥ 1.4 ሚሊዮን የቁም እንሰሳት ህገወጥ በሆነ መንገድ ከሃገራችን እንደሚወጣ ጥናቱ ያረጋግጣል፡፡ የህወሃት የጦር አበጋዞች መንግስት በትግራይ፣በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሱማሊያ በደቡብ ክልሎች በኩል ከኢትዮጵያ ድንበር ዘለል የቁም እንስሳት ንግድ ወደ ሱዳን፣ ሱማሊያ፣ ጅቡቲ፣ ኬንያና ኤርትራ በመላክና በመሸጥ ዳጎስ ያለ የውጭ ምንዛሪ ዶላር በውጭ ሃገራት ባንኮች የዘረፈውን ያስቀምጣል፡፡

በተለይ በአማራ ክልል በኩል ወደ ሱዳን የቁም እንስሳቶች በድንበር በኩል ይሸጣሉ፡፡በ 2007 እኤአ 100000 (መቶ ሽህ) ቁም ከብቶች በህጋዊና ህገ ወጥ መንገዶች ድንበር ተሻግረው ተሸጠዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ 40 በመቶ ሚሆነው በህጋዊ መንገድ በውጪ ንግድ በኩል የተሸጡ ሲሆኑ 60 በመቶው በህገወጥ መንገድ የተከናወነ ንግድ ነበር፡፡ በ 2005 እኤአ 50 በመቶ ህጋዊውና የህገወጡ የውጪ ንግድ ድርሻ ነበራቸው፡፡ 90 በመቶ የሚሆነውን የቁም እንስሳት የውጪ ንግድ የሚያከናውኑት አርቢዎቹ ሲሆኑ ከኢትዮጵያ ድንበር ወደ ሱዳን ሀገር ወስደው በኢትዮጵያ ብር ይሸጣሉ፡፡ የሱዳን የገቢ ንግድ ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በዶለር የቁም ከብቶች ገዝተዉ ይመለሳሉ፡፡ በአማራ ክልል የውጪ ንግድ ቀረጥ ለሱዳን ነጋዴዎች የለም፡፡ በሌላ በኩል በሱዳን በኩል ከፍተኛ የቁም ከብቶች ቀረጥ ማለትም 400 ብር በአንድ ከብት የሱዳን መንግስት የኢትዮጵያን ነጋዴዎች ግብር ያስከፍላል፡፡ ህወሃት የጦር አበጋዞች በዚህ ሕገወጥ ድንበር ዘለል የቁም እንስሳቶች የውጪ ንግድ ተጠቃሚዎች በመሆን ዳጎስ ያለ በመቶ ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር ሃገሪቱ ኪሳራ ደርሶባታል፡፡ የጦር አበጋዞች በውጭ ሃገራቶች ዶለር በማስቀመጥና የሃገሪቱን የውጭ ንግድና የውጪ ምንዛሪ በመዝረፍ ስራ ላይ በመሳተፍ ሃገራችንና ህዝብን ለርሃብ ለበሽታና ለስደት መዳረጋቸውን ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ በተረፈ ከድህረ-ገፁ ቀሪውን ያንብቡ፡፡

Challenges to Ethiopia’s cattle and beef chain By Carina PerkinsCarina Perkins, 04-Jul-2013

የቁም እንሰሳት፣ኢትዮጵያ ከቁም እንስሳ ንግድ በ 2008 ዓ/ም ከ 535 ሽህ በላይ የቁም እንሰሳት ለውጪ ገበያ በመላክ 148 ሚሊን ዶላር አግኝታለች፡፡ በ 2009 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት የተገኘው ገቢ 36 ሚሊዩን 360 ሽህ ዶላር መሆኑ ታውቋል፡፡ የወያኔ የጦር አበጋዞች መንግሥት ህገወት የቁም እንስሳት ንግድን ውስጥ በመሳተፍ ከፍተኛ ገቢ ያገኛል፡፡ ከብቶቹ በተለያዩ ክልሎች ድንበር በኩል፣በሱዳን፣ሱማሊያ፣ ኬንያና፣ጅቡቲ በኩል በእግር እየተነዱ ከአገር እንደሚወጡና በዚህ ድንበር ዘለል በህገ-ወጥ ንግድ ህወኃት ከፍተኛ ዶላር ያገኛል፡፡

ህወሓት የጦር አበጋዞች መንግሥት በ 2008 ዓ/ም ብቻ የቁም እንሰሳት፣ በኮንትሮባንድ ንግድ ከአገር ሊወጡ ሲሉ 5,793,731 (አምስት ሚሊዩን 793 ሽህ 731) እንደተያዙ ሲገለፅ፣ በአገራችን መንግሥት አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ የኮንትሮባንዱ ንግዱ ዋናው ምክንያት የውጪ ምንዛሪ ዶላር ለማግኘት እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ህወሓት የጦር አበጋዞች መንግሥት ‹‹ጀነራል መኮንኖች›› እና የትግራይ ክልል መንግሥት በሱማሊያ፣ በደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ ጅቡቲ፣ ኬንያ በኩል የቁም እንስሳት ንግድ፣ ወርቅ

መዕድን ንግድ፣ የግብርና ምርቶች ንግድ፣ የጫት ንግድ፣የቅባት እህሎች ንግድ ላይ ዋነኛዎቹ ተሳታፊዎች በመሆናቸው በኮንትሮባንድ ንግድ ፎቅ ይገነባሉ፡፡ በኢትዩጵያ የኮንትሮባንድ ገቢና ወጪ ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ዘረፋው እየጨመረ መጥቶል፡፡

{4}የኢትዩጵያና የሱዳን የመሬት ይገባኛል ጥያቄ፣Ethiopian-Sudanese border

የኢትዩጵያና የሱዳን የመሬት ይገባኛል ጥያቄ 1600 ኪሎሜትር ርዝመትና ከ 20 እስከ 60 ኪሎሜትር ስፋት ያለው ቦታ የወያኔ የጦር አበጋዞች መንግስት ለሱዳን መንግስት ለመስጠት ተስማማ፡፡ በዚህም የጎንደር፣ጎጃም፣ወለጋና ኢሉባቡር የነበሩ ግዛቶች ወደ ሱዳን ይገባሉ ማለት ነው፡፡

“This land mass span 1,600 kilometers in length and 20 to 60 kilometers in breadth. All of the country’s ethnicgroups will be affected by this treachery. Good and mutually beneficial neighborly relations between the Ethiopian and Sudanese people will be affected for generations to come. ”

“According to the Tribune “Al-Fashaga covers an area of about 250 square kilometers and has about 600,000 acres of fertile lands. Also there are river systems flowing across the area including Atbara, Setait and Baslam rivers.”
“The issue mainly affects the regions of Gondar, Gojam, Wolega, and Ilubabor. In stating the outlandish, the Sudanese are trying to create a wedge between the Amhara nationality and the rest of Ethiopians. ”

{5}የወደብ አገልግሎት ክፍያ ወጪ፣

ኢትዩጵያ 85 በመቶ የሚሆነውን የውጪና ገቢ ንግድ በጂቡቲ ወደብ በኩል በመጠቀም እስከ 3 ቢሊዩን ዶላር ወጪ ታደርጋለች፡፡ የጂቡቲ መንግስት ወደ ኢትዩጵያ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ አዲስ ክፍያ ማለትም ዕቃዎቹን በዘመናዊ መሣሪያ በመፈተሽ በአንድ ኮንቴይነር ዕቃ፣ ከአስር እስከ 35 ዶላር ለማስከፈል አዲስ ዕቅድ አውጥቶል፡፡ ሃገሪቱ ለጅቡቲ የወደብ አገልግሎት የምትከፍለው በአመት ከ 2.5 እስከ 3 ቢሊዩን ዶላር መክፈል አትችልም፡፡

{6} በህወሃግ/ኢህአዴግ ዘመነ አገዛዝ የንዋይ ኩብለላ (Capital flight)
Year
1991
1992
1993
1994
1995
1996
1997
1998
1999
2000
Capital
Flight
538
-590.5
-327.9
226.0
139.5
26.8
614.9
456.5
-675.6
406.2
Year

2001
2002
2003
2004
2005
2006
2007
2008
2009
2010
Capital
Flight
2518.0
3073.4
1598.4
1400.8
-319.9
104.0
1695.6
-263.8
1875.1
3407.7

Source: Source: Authors' computation.(Capital Flight from Sub-Saharan African Countries: Updated Estimates,1970-2010)

በአጠቃላይ ከ 1991 እስከ 2010 እኤአ በህወሃግ/ኢህአዲግ ዘመን አገዛዝ፤ በህገወጥ መንገድ ከሃገር ውስጥ የወጣ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ 15,903.2 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር ከኢትዮጵያ ረሃብተኛ ህዝብ ተሰርቆ ወደ ተለያዩ ባህር ማዶ አገራት ተቀምጦል፡፡ በህወሃግ/ኢህአዲግ ዘመን አገዛዝ ከ 2014 እስከ 2015 እኤአ በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ 10 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር የንዋይ ኩብለላ/ የተሰረቀ ገንዘብ ከሃገር ውስጥ ወደ ውጭ አገራት ተዘዋውሮል፡፡ከህዝባዊ አብዮቱ በኃላ ደግሞ ካፒታልና የንዋይ ኩብለላ ዘረፋው ተጦጡፎል ሆኖም በዚህ መልክ የተገኘ ሃብት ወደ ደሃ ሃገራቶች መመለሳቸውና ወንጀለኞቹም ወደ ሃገር መመለሳቸው አይቀርም፡፡

{7}የውጭ ዕዳ ክፍያ

በ 2007 እኢአ የኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስት በጀት 178.6 ቢሊዩን ብር ሆኖ በፓርላማ እንደፀደቀ ሲገለፅ ከዚህም ውስጥ የአመቱ የውጭ ዕዳ ክፍያ 8.2 ቢሊዩን ብር እንደሆነ ተገልፆል፡፡ኢትዮጵያ ዕዳውን ለመክፈል በዓመት 8.2 ቢሊዩን ብር እየከፈለችና ሌላ ገንዘብ ሳትበደር እዳዋን ለመጨረስ ከ 45 ዓመታት እስከ 68 አመታት ይፈጅባታል፡፡ በ 2008 እኢአ የኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስት ባጀት 223.3 ቢሊዩን ብር ከዚህም ውስጥ በሶስተኛ ደረጃ ላይ ከሃገሪቱ ባጀት ትልቁን ድርሻ የያዘው፣ የአመቱ የውጭ ዕዳ ክፍያ 11.903 ቢሊዩን ብር እንደሆነና ተገልፆል፡፡ የውጪ እዳ ክፍያው ከ 2007 ዓ/ም በጀት በ 3,703,000,000 ቢሊዩን ብር ከፍ እንዳለ የአሃዙ ስሌት ያሳያል፡፡ በ 2009 እኢአ 274.3 ቢሊዩን ብር በጀት ቀርቦ ከዚህ ውስጥ 13.9 ሚሊዩን ብር የተያዘው ለውጭ ዕዳ ክፍያ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የኢትዮጵያ የፌዴራል መንግስት በጀትና የአመቱ የውጭ ዕዳ ክፍያ
ዓመት(በኢትዩጵያ አቆጣጠር)
መንግስት
በጀት (ቢሊዩን ብር)
የአመቱ የውጭ ዕዳ ክፍያ (ቢሊዩን ብር)
ዕዳ የበጀት በመቶኛ
2007
178.6
8.2

4.6
2008
223.3
11.9
5.3
2009
274.3
13.9
5.1

የኢትዮጵያ የውጪ ብድር ክምችት ከብሄራዊ አማካይ ጠቅላላ አመታዊ ምርት ድርሻ በ2011 እኤአ 19.9 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2014 እኤአ 27 በመቶ ነበር፡፡ የመንግሥታዊ ልማት ዘርፎች ብድር ከብሄራዊ አማካይ ጠቅላላ አመታዊ ምርት ድርሻ በ2011 እኤአ 20.9 በመቶ የነበረ ሲሆን በ2014 እኤአ 42.0 በመቶ ሆኖል፡፡

በ2016/17 እኤአ የህወሓት መንግስትና ብሄራዊ ባንክ ባለሞሎች የሃገሪቱን ልትወጣ በማትችለው የውጪ ብድር ክምችት ከተው ኢኮኖሚውን አዘቅት እንደሚከቱት አጥኝዎች ተንብየዋል፡፡ ለዚህም ግልፅ ማሽረጃ የ2009 ዓ/ም ዓመት እቅድና አፈጻጸም፣ በተለይ የውጪ ንግድ ገቢ ማሽቆልቆል፣ የውጪ ብድር መክፈል አቅም መሽመመድና የውጪ ምንዛሪ እጥረት በቀጣይነት ተከስቶል፡፡ በ2008 ዓ/ም የውጭ ዕዳ ክፍያ 1 ቢሊዩን ዶላር ለመክፈል ተገዶል፡፡ የወለድ ክፍያው በዓመት ከ350 ሚሊዩን ዶላር ከፍ ብሎል፡፡

ለማጠቃለል የኢትዮጵያ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) አነስተኛ መሆን ምክንያት የሃገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት፣ በተቆለለ የውጭ ብድር ክምችትና የእዳ ክፍያ ምክንያት በረጅም ግዜያት ውስጥ እንደሚናጋ ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጵያ የውጭ ብድር በ1975 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 343.7 ሚሊዩን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 14% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ በ1991 እኤአ የኢትዮጵያ የውጭ ብድር 9.1 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 214% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ በጁን 30 1999 ይሄ አሃዝ 10.2 ቢሊዬን ዩኤስ ዶለር ከፍ ብሎል፡፡በ2011 እኤአ የኢትዬጵያ የውጭ ብድር 7.102 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) 23.5% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ 2012 እኤአ የኢትዬጵያ የውጭ ብድር 12 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት (GDP) –% እጅ ይይዝ ነበር፡፡ 2013 እኤአ የኢትዬጵያ የውጭ ብድር 16.11 ቢሊዩን ዩኤስ ዶለር የነበረ ሲሆን ይህውም አመታዊ አጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት($46) ቢሊዬን ዩኤስ ዶለር (GDP) 35% እጅ ይይዝ ነበር፡፡

ለቻይናዎች ጭፍራ፣ ለሱዳን ቡችላ
አይገዛም ህዝቡ፣ ከዛሬ በኃላ፤
አይገዛም፣ አይገዛም፣ አይገዛም!!!
ለአንባገነን መንግሥት፣ህዝቡን ላልወከለ
አይገዛም ህዝቡ ሳለ እየታገለ፣
አይገዛም፣ አይገዛም፣ አይገዛም!!!
ለወያኔ ዘር ቆጣሪ፣ አበጋዞች
ለወያኔ አጥር አጣሪ፣ ጦረኞች
ለወያኔ ሙሰኛ፣ ወንጀለኞች
አይገብሩም የኢትዩጵያ ልጆች!!!
በወያኔ ፋሽስት፣ የተሠው ሁሉ፣
አትረሱም ፉፁም፣ ተከታዩች አሉ!!!
አይገዛም፣ አይገዛም፣ አይገዛም!!!
ይህ ህዝባዊ መዝሙር በኢትዩጵያ ምድር ከአጥናፍ አጥናፍ ይዘመራል፡፡

የህወኃት ጦር ሠራዊት ከተለያዩ የክልል መንግሥቶች ውስጥ ይውጣ!!!
የአጋዚ ጦር ወደ ደደቢት ካንፑ ይመለስ!!!
የህወኃት ጦር ሠራዊት ድንበሩን ይጠብቅ!!!

## ምንጭ

1-The Ethiopia Herald, December 2, 2014

2- NBE to Print Banknotes in Ethiopia, Bank plans to cut foreign currency spending by printing banknotes in Ethiopia gov_of_nbe_teklewold_atnafu Published on December 14, 2014 [ Vol 15 ,No 763]

3-© 2017 Sudan Currency Printing Press

4- NBE to print birr notes in Sudan, By Staff Reporter – July 30, 2013